የሰ/መ/ቁ. 59979

የካቲት 9 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች ፡-** የኦሮሚያ መንገዶች ባለሥልጣን - ሠላማዊት ሀይሉ - ቀረቡ

**ተጠሪ ፡-** አቶ ከበደ ወዳጆ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በወሮጉድሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ ለሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ በከሳሽነት ቀርቦ አመልካች (ተከሳሽ) በጅማ ገነት ወረዳ ውስጥ የገጠር መንገድ ሲጠግን አላግባብ በእርሻ መሬት ይዞታዬ በመግባት የተለያዩ ቋሚ አትክልቶች የሰብል ምርትና ሣር ቤት አውድሞብኛል፡፡ ተከሳሽ በቆፈረው ጉድጓድ በሬ ገብቶ ስለሞተብኝ የበሬውንም ዋጋ እንዲከፍለኝ በማለት በአጠቃላይ የጉዳቱን መጠን ብር 71950 ብር በመገመት ካሳ እንዲከፈለው ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ የይርጋ ጊዜው አልፏል፡፡ ሥራ ያሠራሁት በክልሉ አዋጅ ቁጥር 11/88 በተሰጠኝ ሥልጣንና ሀላፊነት መሠረት ነው፡፡ ከሳሽ አሉ የሚሏቸው ንብረቶች በቦታው ላይ አልነበረም፡፡ የበሬ ዋጋ ልንከፍል አንገደድም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች (ተከሳሽ) በተጠሪ ይዞታ ሥር የነበሩ ግምታቸው ብር 7,850 (ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ሀምሳ ብር) ያላቸው የተለያዩ ተክሎች አውድሟል፡፡ የከሳሽ(ተጠሪ) በሬ ተከሳሽ ከቆፈረው ጉድጓድ ገብቶ የሞተ ስለሆነ ብር 2,500 (ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር) በጠቅላላው ብር 10,350 (አስር ሺ ሶስት መቶ ሀምሳ ብር) አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ይዞታው የተጠሪ ይዞታ መሆኑ በተጠሪ ይዞታ ላይ ያለው ተክል ላይ አመልካች አላግባብ ጉዳት እንዳደረሰ የተረጋገጠ መሆኑ ስለተረጋገጠ አመልካች ለተጠሪ ብር 7,750 (ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ ብር) እንዲከፍል የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው፡፡ አመልካች

የበሬ ዋጋ ግምት ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ያቀረበ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች ጳጉሜ 2 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2143ን በመጥቀስ ያቀረብነውን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ ያደረገው አላግባብ ነው፡፡ በመሬቱ ላይ አትክልትና ንብረት እንደሌለ ተረጋግጦ እያለና በአዋጅ በተሰጠኝ ሥልጣን መሠረት መንገድ የጠገንኩ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ካሣ እንድንከፍል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የጠቀሳቸው የይርጋ ድንጋጌዎች ማለትም የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1149(1) እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2143 በእኔና በአመልካች መካከል ባለው ክርክር ተፈፃሚነት የላቸውም፡፡ አመልካች በህጋዊ ይዞታዬ ላይ በነበሩት ቋሚ አትክልቶች ላይ ጉዳት ማድረሱ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች ለህዝብ ግልጋሎት የሚሰጥ የመንገድ ጥገና ሥራ በሚያከናውንበት ወቅት የተጠሪን ይዞታና በተጠሪ ይዞታ ላይ ያሉ የተለያዩ ተክሎች ላይ ጉዳት ስላደረሰ ካሣ እንዲከፍላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ከውል ውጭ የሚደርስ ሀላፊነትን የሚመለከት ክስ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ጥያቄ አመልካች ይዞታውን ለህዝብ ጥቅምና ግልጋሎት የሚውል መንገድ ለመጠገን ከወሰደ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 8 መሠረት በይዞታው ላይ ለነበረው ንብረት ተመጣጣኝ ካሣ የመክፈል ሀላፊነት አለበት፡፡ ስለዚህ በመሬቱ ላይ የነበሩትን ተክሎች ዋጋ ይክፈለኝ የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ በህገመንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 8 መሠረት ለተወሰደ ንብረት ካሣ እንዲከፈላቸው ተጠሪ የመጠየቅ መብት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1149 ንዑስ አንቀፅ 1 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2143 ንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገገው የሁለት ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ የማይገደብ መሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 42629 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተጠሪ ክስ በሁለት ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ አይታገድም በማለት የሰጡት ውሣኔ ተገቢና መሠታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ በይዞታ መሬቴ ላይ ነበሩ ከሚላቸው የተለያዩ አይነት ቋሚ ዛፎችና አትክልቶች ጠቅላላ ግምት ከብር 60,000(ስልሣ ሺህ ብር) በላይ እንደነበርና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣናቸውን ተጠቅመው በተጠሪ ይዞታ ላይ የነበሩትና በአመልካች ጉዳት የደረሰባቸው ተክሎችና ዛፎች ግምት 7,750 (ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ ብር) መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች ይህንን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል ወስነዋል፡፡ አመልካች በቦታው ላይ ምንም አይነት ንብረት የለም በማለት በሰበር አቤቱታው የሚከራከር ቢሆንም ይህ የአመልካች ክርክር የፍሬ ነገር ክርክር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም አመልካች የካሣውን መጠን በተመለከተ ያቀረበው አቤቱታ ለሰበር ችሎት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 ከተሰጠው ሥልጣን ውጭ የቀረበና ሕጋዊ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

በአጠቃላይ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ጥቅምት 26 ቀን 2003 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ